# በሙስኞች ላይ የተወሰደው እርምጃ ኪራይ ሰብሳቢነትን የመዋጋት ስትራቴጂ አካል ነው

ክፍል አንድ

ኢብሳ ነመራ 05/24/13

የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽን ከአንድ ሣምንት በፊት ሁለት ከፍተኛ የፌዴራል መንግስት ባለሥልጣናትን - የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና ዳየሬክተረና ምክትላቸውን በሙስና ወንጀል ጠርጥሮ በቁጥጥር ሥር አውሏል፡፡ ከእነዚህ ከፍተኛ ባለሥልናት ጋር ሌሎች የየጉምሩክና የአገር ውስጥ ገቢ የሥራ ኃላፊዎችና ነጋዴዎቸ በጠቅላላው 54 ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር ውለዋል፡፡ ተጠርጣሪዎቹ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁለተኛ ወንጀል ችሎት ቀርበው ክስ ለመመሥረት የግዜ ቀጠሮ ተጠይቆባቸዋል፡፡

ይህን ተከትሎ ጉዳዩ ከፍተኛ የመገናኛ ብዙሃንን ትኩረት ስቧል፡፡ ከተራው ዜጋ ጀምሮ በረካታ ሰዎች በጉዳዩ ላይ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ አስተያየት ከሰጡት መሀከል በውጭ አገር የሚገኙ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ እንቅስቃሴ ቀላጤዎችና በአገር ውስጥ የሚገኙ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፖርቲ አመራሮች ይገኙበኝታ፡፡

በአገር ውስጥ በዜጎች የተሰጡት አስተያየቶች መንግሥት ሙስናን ለመቆጣጠር የሙስና ውንጀል ፈጽመዋል ያላቸውን ተጠረጣሪዎች በቁጥጥር ሥር መዋሉ የሚደነቅና የሚመሰገን በጎ እርምጃ መሆኑን የመላከቱ ናቸው፡፡ በተቃዋሚዎች የተሰጡት አስተያየቶችም ቢሆኑ እርምጃውን ሙሉ በሙሉ የሚቃወሙ ባይሆኑም ብዥታ የሚፈጥሩ ሃሳቦች ስላዘሉ በውጭና በአገር ቤት ከተሰጡት አስተያየቶች አንድ ሶስቱን ለይቼ ልመለከታቸው ወድጃለሁ፡፡ ከወደ ውጭው ልጀምር፡፡

የኢትየጵያን ጉዳይ አንዳንዴ ከአሜሪካ መንግስት አቋም ጋር የሚጻርር በሚመስለን ሁኔታ ያለወጉ ጠምዝዞ በማራገብ የሚታወቀው የአሜሪካ ድምጽ የአማርኛ ፕሮግራም ግንቦት 9፣ 2005 ዓ/ም “እሰጥ አገባ” በተሰኘው ፕሮግራሙ በሙስና ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የዋሉ

ከፍተኛ የመንግስት ሃላፊዎችን መነሻ በማድረግ በውጭ ያሉ ተቃዋሚዎችን ቀላጤዎች አስተያየት አስደምጦናል፡፡ ከእነዚህ መሃከል በማንኛውም ኢትዮጵያ ውስጥ በሚነሳ አጀንዳ ላይ "ከእኔ በላይ አዋቂ ላሳረ" ባዩ ጀዋር መሃመደ የተባለ ወጣት "ተንታኝ" ይገኝበታል፡፡ እኔም በዚሁ ጀዋር በሰጠው አንድ አስተያየተ ላይ አተኩራለሁ፡፡ በቅድሚያ ግን እዛም እዚህም አለሁ የሚለው ጃዋር በኢትዮጵያዊያን ዘንድ በተለይ በወጣት ልሂቃን እንዴት እንደሚታይ በአጭሩ ላነሳ፡፡

ጀዋር መሃመድ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር አባል የነበረ ግለሰብ ነው፡፡ ከኦሮሞ ሕዝብ ፍቃድና ውሳኔ ውጭ ኦሮሚያ ነጻ መንግስት ምሆኗን ይደግፋል ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የዘውዳዊው ስርአት አይነት አሃዳዊ ስርአት ለመመስረት ለሚንቀሳቀሱትም፣ ልእስላማዊ እንቅስቃሴም በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕገመንግስታዊ ስርአት ላይ በማንኛውም ምክንያት ተቃውሞ ያነሱ ወገኖችን በሙሉ ለማገልገል ዝግጁ ነው፡፡

እርግጥ ጀዋር ብዙ መጻሕፍት አንብቦ፣ በርካታ መረጃዎችን ቃርሞ ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ በፍልስፍና መርሕ ማሰብ ስላልጀመረ፣ ከቃረማቸው መረጃዎች ያገኘውን የመረጃ እውቀት(perception) ነው እንደወረደ የሚተፋው፡፡ ለዛውም ራሱ በወጉ ካልፈተሸው ጭፍን የጥላቻ ስሜት ተነስቶ፡፡ እርግጥ ወጣት ጀዋር ለወደፊት ሊበራ የሚችል መሆኑ በግልጽ ይታያል፡፡ አሁን ግን "ከፈረሱ ጋሪው ቀደመ" እንዲሉ ከመብራቱ በፊት ማውራቱ ቀደመና ከማሳወቅ ይልቅ ማደናገሩ አየለ፡፡

ያም ሆነ ይህ በግለሰቡ ላይ ያለውን አተያይ በዚሁ ትቼ ሰሞኑን መንግስት በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የዋሉትን ሰዎች መነሻ በማደረግ በአሜሪካ ድምጽ የአማርኛ ፕሮግራም ላይ ወደሰጠው አስተያየት ልመለስ፡፡ ይህም ከአገር ውስጥ በሕገ ወጥ መንገድ ይወጣል ያለውን የውጭ ምንዛሪ ገንዘብ የሚመለከት ነው፡፡

ጀዋረ በሰጠው አሰተያየት " አገራችን በየአመቱ ወደ 40 በመቶ የሚሆነውን ባጀት በድጎማና በእርዳታ ታገኛለች፣ ውጭ አገር ያለው ዜጋ ደግሞ ወደ 2 ቢሊየን ዶላር ይልካል፡፡ ይሁን እንጂ በአመት ወደሶስት ቢሊያን ዶላር የሚሆነው ተመልሶ በህገ ወጥ መንገድ ይወጣል፡፡" ብሎናል፡፡

ጃዋር ለአገር ሃብት ብክነት ያሳየውን ተተቆረቋሪነት እያደነኩ፣ በቅድሚያ በተለይ ከሃገር ውስጥ በህገ ወጥ መንገድ ይወጣል ብሎ የጠቀሰውን የ3 ቢሊየን ዶላር መረጃ ከየት እንዳገኘው ምንጭ ስላልጠቀሰ፣ ጠቅሶ ቢሆንም ማንም የመቸኛል ባለው መንገድ አገሩ ቁጭ ብሎ የፈቀደውን

በሚያወራበት ዘመን ይፋ የተደረጉ መረጃዎች በሙሉ የማይታመኑ በመሆናቸው የመረጃው ትክክለኝነት አጠራጣሪ ነው፡፡

እርግጥ ኢትየጰያን መነሻ ያደረገ የውጭ ምንዛሪ ወደ ውጭ የሚወጣ መሆኑ እውነት ነው፡፡ ይህ የውጭ ምንዛሪ ግን በሕጋዊ መንግድ ወደአገርውስጥ ገብቶ በአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ቋት ውስጥ የተከማቸ ሳይሆን በሕገወጥ መንገድ የዘለቀና ወደአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ቋት ያልገባ ነው፡፡

በተለይ ውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ወደ አገር ቤት ገንዘብ የሚልኩት በአብላጫው  በሕገወጥ መንምገድ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ ጃዋር በቀላጤነት የሚያገለግላቸው ጽንፈኛ ተቃዋሚዎች ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡

በተለየ ጃዋር በሚኖርባት ሰሜን አሜሪካ የሚገኙ ኢትዮጰያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ገንዘብ በሕጋዊ መንገድ እንዳይልኩ እስከዛቻና ማስፈራራት የዘለቀ አሳፋሪ ቅስቀሳ ሲደረግ እንደነበረ እናውቃለን፡፡ በብር ተመንዝሮ ተመልሶ ወደውጭ የሚወጣው ይህ የውጭ ምንዛሪ መሆኑን ልብ በሉ፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ መወቃቀስ ካለብን ዋነኞቹ ተወቃሾች እነጃዋር ራሳቸው ናቸው፡፡ ወጣት ጃዋር ኢትዮጵያ ውስጥ የቅርብ ዘመዶች አላቸው ብዬ እገምታለሁ፡፡ ታዲያ ለእነዚህ ዘመዶቻቸው ገንዘብ መላካቸውም አይቀሬ ነው፡፡  ገንዘብ የሚልኩት በየትኛወ መንገድ ይሆን? ይህ ጥያቄ ሁሉንም የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ይመለከታል፡፡

ለምሳሌ ሰሞኑን በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር ከዋሉት መሃከል የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ምክትል ዋና ዳየሬክተር የነበሩት አቶ ገብረ ዋሃድ ገብረ ጊዮርጊስ መኖሪያ ቤታቸው ሲበረበር የተገኘው 19 ሺህ ዩሮ፣ ተመሳሳይ መጠን ያለው ፓውንድ ከብሄራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ ቋት የተመነዘረ ሳይሆን በሕገወጥ መንገድ ከገባ ላይ የተመነዘረ መሆኑ እርግጥ ነው፡፡

እናም ጃዋር በዚህ ዙሪያ  የሰነዘረው ትችት ትክክለኛነቱ ያልተረጋገጠ አሃዝ ላይ የተመሰረተ እና/ወይም በአገሪቱ ካለው ነባራዊ የውጭ ምንዛሪ ሁኔታ አኳያ ያለተመዘነ አዋቂ ነኝ በሚል ግብዝነት የተሰነዘረ ነው፡፡

ወደ አገር ውስጥ ስንመለስ በተመሳሳይ ገዳይ ላይ አሰተያየት ከሰጡት የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች መሃከል ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ አንዱ ናቸው፡፡ ፕ/ር በየነ ግንቦት 10፣ 2005 ዓ/ም የአዲስ አደማስ ጋዜጣ እትም የሰጡት አስተያየት መንግሥት ሰሞኑንና ቀደም ሲልም በሙስና ወነጀል ተጠርጣሪዎች ላይ የወሰዳቸው እርምጃዎች ላይ ብዢታ የሚፈጥሩ ሆኖ አግቼዋለሁ፡፡

የአዲስ አድማሰ ጋዜጠኛ ፕ/ር በየነን ማናገረ የጀመረው "ከዚህ ቀደም ፖርቲያችሁና አመራሮቹ መንግሥትን በሙስና ሲተች ቆይቷል፡፡ በተለይ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት ላይ ከማተኮር ይልቅ ትናንሽ ሙሰኞች ላይ ያተኩራል ስትሉ ቆይታቹሃል፡፡ ሰሞኑን በገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ላይ የተወሰደው እርምጃ የትችታችሁና የምክራቸው መውጤት ነው ማለት ይቻላል" በሚል ጥያቄ ነበር፡፡

ፕ/ር በየነ ለዚህ ጥያቄ በሰጡት ምላሽ "እርምዳውን የገዘፈን ነገር እንዲሁ መነካካት ነው" ብለዋል፡፡ ይህንንም ሲያብራሩ "እህአዴግ አባሎቹና ደጋፊዎቹ ለሚላቸው አገርን እንዲበዘብዙ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ከዚህ አንፃር የሠሞኑ እርምጃ መነካካት ነው፡፡ ዋናወን የሙስና ሰንሰለት ለመበጣጠስ የጀመረው እንቅስቃሴ ነው ለማለት ገና ነው" ብለዋል፡፡

በቅድሚያ "መንግሥትን በሙስና የተዘፈቀ ነው በማለት በተደጋጋሚ ትችት ሥትመነዝሩ ነበር" በሚል በጋዜጠኛው የቀረበው ጥያቄ ራሱ ፕ/ር በየነንና ፓርቲያቸውን አይመለከትም ባይ ነኝ፡፡ የፕ/ር በየነ ፓርቲ ሙስናን የመዋጋት ጉዳይ በአጋጣሚ፣ በአብዛኛው ሌላ መንግሥትን የሚያሣጡበት ሰበብ ሲያጡ የሚያነሱት እንጂ ስራዬ ብለው መክረው አቋም የያዙበት ጉዳይ አይደለም፡፡ ሙስናን በተመለከተ "ችግሩ ምን ያህል አስከፊ ነው? ሙስናን ለመከላከል ምን መደረግ አለበት?" የሚለው ላይ አቋም ይዘው መግለጫ አውጥተው አያውቁም፡፡ ስለዚህ "ሙስናን ለመከላከል ምክር ሰጥታቹሃል" የሚለው አይመጥናቸውም፡፡

ፕ/ር በየነ ወደሰጡት ሌሎች አስተያየቶች ስመለስ፣ እርሳቸውም እንዳሉት በአገራችን ሙስና መስፋፋቱ እውነት ነው፡፡ መንግሥትና ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ይህን ተገንዝበዋል፡፡ ኢህአዴግ "ኪራይ ሰብሳቢነት የስረአቱ አደጋ ነው" የሚል አቋም ይዞ ይህን በተደጋጋሚ በይፋ ሲገልጽ መቆየቱን ሁሉም ዜጎቸ ያውቁታል፡፡ እንደ ፓርቲ በሥራ አስፈፃሚና በማእከላዊ ኮሚቴ ደረጃ በሚያደርጋቸው መደበኛ ስብሰባዎች፣ እንዲሁም በየሁለት አመት ከመንፈቅ የሚያካሂደው ድርጅታዊ ገባኤ ላይ ሙስናንና መልካም አስተዳደርን በተመለከተ በሥፋትና በጥልቀት ሲመክር፣ አቋም ሲይዝ ነው የቆየው፡፡

የኢፌዴሪ መንግሥት ተመሥርቶ ሁለት አመት እንኳን ሳይሞላው በ1989 ዓ/ም የግንባሩ ምክትል ሊቀመንበርና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ነበነበሩት አቶ ታምራት ላይኔ "የሙስና ወንጀል ፈጽመዋል" ለማለት የሚያስችል ማስረጃ ስላገኘባቸው ይህን በይፋ በማሣወቅ በፍርድ ቤት ክስ እንደመሠረትባቸው አዱርጓል፡፡ ተጠርጣሪው አቶ ታምራት ፍርድ ቤት የቀረበባቸው ማስረጃ ጥፋተኝነታቸውን በማረጋገጡ የ18 ዓመት ቅጣት ተወስኖባቸው ቅጣታቸውን ፈጽመው ተለቀዋል፡፡

ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግና መንግስት ሙስናን በመከላከል ላይ ያላቸው ቁርጠኛ አቋም በ1993 ዓ/ም የሥነምግባርና የፀረሙስናን ኮምሽን በማቃቋም ተገልጿል፡፡ ይህን ተከትሎ ሙሰና በባሕሪው የተለየ ወንጀል በመሆኑ የፀርሙስና ሕግ እንዲወጣ አድርጓል፡፡

ከዚህ በኃላ የኢህአዴግ ከፍተኛ አመራርና የሽግግር መንግስቱ የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ሥዬ አብርሃን ጨምር ሌሎቹ የፌዴራልና የክልል ከፍተኛ ባለስልጣናት ላይ ክስ በመመስረት እንዲቀጡ ተደርጓል፡፡ አሁንም በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው ክስ ተመስርቶባቸው የፍርድ ሂደታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ የፌዴራል መንግስት ከፍተኛ ባለሥልጣን የሆኑ ግለሰብ አሉ፡፡ እርሳቸውም የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልላዊ መንግስት ርእሰ መስተዳድር የነበሩትና በኋላም የፌዴራል የሕብረት ሥራ ማህበራት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ሆነው ተሹመው የነበሩት አቶ ያረጋል አይሸሹም ናቸው ፡፡

ሠሞኑን በፌዴራል የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተርና የብአዴን ማእከላዊ ኮሚቴ አባል አቶ መላኩ ፈንታ እንዲሁም የኤህአዴግ ታጋይና አባል በሆኑት በምክትል ዋ/ዳይሬክተሩ አቶ ገ/ዋሃድ ወ/ጊዮርጊስ ላይ የተወሰደውም እርምጃ እንዲሁ መንግሥትና ገዢው ፓርቲ ሙስናን ለመከላከል ያላቸውን ቁርጠኝነት በግልጽ ያሣያል፡፡

ሙስና በአገራችን መስፋፋቱ እውነት ቢሆንም፣ ከሃያ አመት ወዲህ የተፈጠረ አዲስ ክስተት አለመሆኑ ሊታወስ ይገባል፡፡ ከቀደሙት ሥርአቶች የተወረሱት ሙስናን የማይጠየፍ - እንደነውር የማይመለከት ባሕል ያስከተለው መሆኑም መዘንጋት የለበትም፡፡

በቀደሙት የዘውዳዊና የወታደራዊ ቡዱን የመንግስት ሥርአቶች የሙስና ጉዳይ የአሁኑን ያህል የአገር አሳሳቢ ጉዳይ ሆኖ ገንኖ ያልወጣው ሙስና ስላልነበረ ሳይሆን፣ ሙስናን መዋጋትና መከላከል ትኩረት ስላልተሰጠው ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የመንግስትና የሕዝቡ የዘወትር የመወያያ

አጀንዳ ለመሆን አልበቃም፡፡ ይህ ማለት ግን አሁን በአገራችን ያለውን ሙስና እንደ ልዩ ጉዳይ መመልከት አያስፈልግም ማለት እንዳልሆነ ልብ እንዲባልልኝ እፈልጋለሁ፡፡